# ቀናችሁ አትርሳኝ!

(ወለላዬ ከስዊድን)

ያልታየን አሟሟት- ባንተ አይቼ

ሞትህን በቁሜ ሞቼ

ሲገድሉህ የተሰበረ ቅስሜ

እስካሁን አልጠገነም ህመሜ

ሲገሉሽ ሞቼ ነው የከረምኩ

ከስቃይሽ እኔም አልተረፍኩ

ይህንን የናንተን አበሳ

ልጽፈው ብዬ ብነሳ

ሀዘን ዘልቆ ከገባ- አጥንት ድረስ

ለካስ ቃላትም- የአንጀት አያደርስ

እዬዬም ሲዳላ ነው ይባላል

እንባም ስቃይ ሲከብደው- ለካስ ይደርቃል

ደርቆ ይቅር- ድሮስ ምን ሊጠቅም እንባ

ቃላትም በኖ ይጥፉ- ያሻው ቦታ ሄዶ ይግባ

ሁለቱስ ምን አባታቸው ሊያደርጉልኝ

ሞታችሁን ብረሳ ግን- ያቺ ቀናችሁ አትርሳኝ።

***

በሳውዲ ዐረቢያ አለምንም ጥፋታቸው ለተጨፈጨፉት
ኢትዮጵያውያን ወገኖቼ መታሰቢያ ይሁን